MY SCHOOL DC
የሕዝብ ት/ቤት ሎተሪ

# ጥያቄዎች በወላጆች ለወላጆች



## መግቢያ

በዲስትሪክቱ ውስጥ በርካታ የህዝብ ትምህርት ቤት አማራጮች በመኖራቸው፣ ወላጆች እና አሳዳጊዎች ልጃቸው የእኔ ትምህርት ቤት (MY SCHOOL) ብሎ የሚጠራውን/የምትጠራውን ትምህርት ቤት ለማግኘት በሚፈልጉበት ጊዜ ትምህርት ቤቶችን የሚጠይቁ የተለያዩ ጥያቄዎች ሊኖሯቸው ይችላል። ከMy School DC የወላጅ አማካሪ ምክር ቤት (PAC) የመጡ የወላጅ ተወካዮች እርስዎን ለማስጀመር እንዲረዱ እነዚህን የጥያቄዎች ዝርዝር አውጥቷል። መሰረታዊ መረጃ ለማግኘት በ MySchoolDC.org የትምህርት ቤት የኦንላይን ፕሮፋይልን ይጎብኙ፣ እና የትምህርት ቤት ሰራተኛን መጠየቅ የሚፈልጉ ጥያቄዎች አጠገብ የምርጫ ምልክት ያስቀምጡ። እነርሱን ወደ EdFEST፣ የትምህርት ቤት ዝግጅቶች እና የትምህርት ቤት መክፈቻ ቤቶች ጭምር ይዘዋቸው እንደሚሄዱ ያረጋግጡ!

## የትምህርት ቤት ፖሊሲዎች እና የድጋፍ አገልግሎቶችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ የበፊት እና የኋላ እንክብካቤን ያቀርባሉ? ለበፊት እና ኋላ የእንክብካቤ ፕሮግራማችሁ እንዴት ማመልከት እችላለሁ?
- ☐ የበፊት እና የኋላ የእንክብካቤ ፕሮግራሞቻችሁ በትምህርት ቤቱ ወይስ በውጭ ድርጅት ነው የምተዳደረው? ፕሮግራም አወጣጡ ከትምህርት ቤት የትምህርት ሥርዓት ጋር እንዴት ይሄዳል?
- ☐ የትምህርት ቤትዎ የበፊት እና የኋላ እንክብካቤ ፕሮግራሞች አቅም ምን ይመስላል? በእርሱ ፍላጎት ላላቸው ሁሉም ቤተሰቦች በቂ ክፍል አለ?
- ☐ የትምህርት ቤትዎ ደንብ ልብሶች ወይም የአለባበስ ኮዶች ምንድን ናቸው? በደንብ ልብሱ ወጪ ቤተሰቦችን ይረዳሉ?
- ☐ ትምህርት ቤትዎን እንደ አማራጭ ለመውሰድ ስናስብ ከግምት ማስገባት ያሉብን የትምህርት ቤትዎ ፕሮግራም ላይ የሚጨመሩ ወጪዎች አሉ?
- ☐ ልጄ የትርፍ ጊዜ ትምህርት ከፈለገ/ች፣ ይገኝላቸዋል? ተጨማሪ ድጋፎችን ለተማሪዎች ለማቅረብ ከውጪ ድርጅቶች ጋር አጋርነት ይፈጥራሉ (ለምሳሌ፣ ከፍተኛ ስኬት፣ የንባብ አጋሮች)?
- ☐ ምን ዓይነት ስፖርቶች፣ ክለቦች፣ እና ሌሎች ከትምህርት ጊዜ ውጪ ተግባራትን ያቀርባሉ? እነርሱ ለሁሉም ተማሪዎች ይገኛሉ፣ ልዩ ፍላጎቶች ያላቸው ተማሪዎችን ጨምሮ? ተማሪዎች እንዲሳተፉባቸው ከእነዚህ ተግባራት ጋር የተያያዙ ወጪዎች አሉ? የተገደቡ ቦታዎች አሉ ወይም ክፍት ቦታ አለ?
- ☐ የበጋ ፕሮግራም አላችሁ? የሚኖራችሁ ከሆነ፣ ምን ወጪ ይጠይቃል? ሾቸሮች ተቀባይነት አላቸው? ለሁሉም ተማሪዎች ይኖራል?
- ☐ የባህሪ ቁጥጥር እና ሥነ-ምግባር ጋር በተያያዘ የትምህርት ቤትዎን ባህል እና ፖሊሲዎችን ግለጹ። ለምሳሌ፣ የተሃድሶ ፍትህ አካሄድ ትጠቀማላችሁ?
- ☐ የክትትል ፖሊሲያችሁ ምንድን ነው?
- ☐ ተጨማሪ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች ጋር ወይም በአጠቃላይ ከቤተሰቦች ጋር የሚሰራ ቁርጠኛ የሆነ የወላጅ ግንኙነት ወይም የወላጅ ተሳትፎ ሠራተኛ ሰው አላችሁ?

## የትምህርት ቤት ትምህርት ሥርዓት የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ የትምህርት ቤታችሁ የትምህርት ሞዴል ምንድን ነው (ለምሳሌ፣ የአዕምሮ መሳሪያዎች)? ልጆቻቸው ስለ ምን እየተማሩ እንደሆነ ወላጆች እንዴት ማወቅ ይችላሉ?
- ☐ የትምህርት ቤታችሁ የትምህርት ፍልስፍና ምንድን ነው እና በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ እንዴት ይገባል? ለምሳሌ፣ እንደ ወሳኝ ውድድር ንድፈ ሃሳብ ወይም ማህበራዊ ፍትህ ዓይነት ጽንሰ-ሀሳቦች በትምህርት ይሰጣሉ?
- ☐ በትምህርት ሥርዓታችሁ ውስጥ ለባህል ምላሽ የሚሰጡ አስተምሮን ታካትታላችሁ? ከሆነ፣ እንዴት አድርጋችሁ?
- ☐ እባክዎ የማህበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርት ላይ የትምህርት ቤታችሁን አቀራረብ ግለጹ።

ተጨማሪ ጥያቄዎች አሉዎት? መልሶች አሉን! የMy School DC ነጻ የስልክ መስመር፥ (202) 888-6336 | info.myschooldc@dc.gov

- ☐ ተማሪዎችን የተለያዩ የስራ-መስኮች እና ቴክኒክ ትምህርት ጋር ለማስተዋወቅ ከውጪ ድርጅቶች ጋር አጋርነት ትፈጥራላችሁ?
- ☐ ለኮሌጅ እና ሥራ-መስኮች ዝግጁነት ግምገማ አጋርነት (PARCC) ፈተና የፈተና ዝግጅት ምን ይመስላል?
- ☐ በትምህርት ቤታችሁ የተለመደው የትምህርት ክፍል የጊዜ ሰሌዳ ምንድን ነው?
- ☐ ልጄ በየቀኑ ለመቀበል መጠበቅ ያለበት/ባት የቤት ስራ ምን ያህል ነው?
- ☐ ትምህርት ቤታችሁየሙያ ስልጠና ፕሮግራሞችን ያቀርባል (ለምሳሌ፣ የእንጨት ሥራ፣ ግንበኝነት፣ የኤሌክትሪክ ሥራ፣ የጸጉር ማስተካከያ ሥራ፣ የቁንጅና ሥራ)? ለእነዚያ ፕሮግራሞች እንዴት ብቁ ይሆናሉ? እነዚህ ፕሮግራሞች ወይም የትምህርት ዓይነቶች ይቆጠራሉ እና የልምምድ ስራ አላቸው?

## የትምህርት ቤት አሰራሮችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ ትምህርት ቤታችሁ የህብረተሰብ ትምህርት ቤት ነው?
- ☐ ትምህርት ቤታችሁ በትምህርት ዓመቱ ስንት ቀን ዝግ ይሆናል? ለምሳሌ፣ የሙያ እድገት ቀን፣ በዓል ቀናት እና እረፍቶች? በእነዚህ ቀናት የልጅ እንክብካቤ ይኖታል?
- ☐ በትምህርት ሥርዓታችሁ ውስጥ ምን ዓይነት ቴክኖሎጂ ትጠቀማላችሁ እና ልጄ እንዴት ይጠቀመዋል/ትጠቀመዋለች?
- ☐ በትምህርት ቤታችሁ የአማካይ የክፍል መጠን ስንት ነው? በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ስንት አዋቂዎች እና ህጻናት አሉ?
- ☐ ትምህርት ቤታችሁ በትምህርት ዓመቱ የመስክ ጉዞዎችን ወይም ተመሳሳይ እድሎችን ያቀርባል?
- ☐ እንደ ትምህርት ሥርዓታችሁ አካል የጂም ክፍለ-ጊዜ ወይም እረፍት ጊዜ ትሰጣላችሁ? ተማሪዎች የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ የመጫወቻ ቦታ ወይም የቤት ውጪ ቦታ አላችሁ?
- ☐ ትምህርት ቤታችሁ የሙሉ-ጊዜ የነርስ ባለሙያ እና አማካሪ ሰራተኛ አለው?

## የወላጅ ተሳትፎን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

- ☐ ትምህርት ቤታችሁ የተቀናጀ የወላጅ መምህር ቅንጅት (PTO) ወይም ተመሳሳይ ቡድን አለው? ከሆነ፣ ስራ ላይ አለው?
- ☐ ወላጆችን፣ ልዩ ፍላጎቶች ያላቸው ልጆች ወላጆች ወይም ኢንግሊዝኛ-ተናጋሪ ያልሆኑ ወላጆችን ጨምሮ፣ በትምህርት ክፍል ውስጥ እንዴት ታሳትፋላችሁ? በትምህርት ቤት ደረጃ?
- ☐ እንደ ጉልበተኝነት እና ሁከት መከላከል ያሉ ጉዳዮች ላይ የትምህርት ቤት ኮሚቴ ወይም ሌሎች የወላጅ ተሳትፎ መንገዶች አሉ?

## ጥያቄዎች ኢንግሊዝኛ ተማሪ ለሆኑ ቤተሰቦች

- ☐ ኢንግሊዝኛ የልጄ የቤት ቋንቋ አይደለም። ልጄ በትምህርት ቤታችሁ እንዲሻሻል/እንድትሻሻል እና እንዲሳከለት/ላት ለመርዳት ምን ዓይነት ድጋፎች ተቀምጠዋል?
- ☐ ትምህርት ቤታችሁ ኢንግሊዝኛ-ተናጋሪ ካልሆኑ ቤተሰቦች ጋር እንዴት ይግባባል እናም መረጃን እንዴት ያጋራል??
- ☐ አስተርጓሚን ወይም ሰነድ ወደ ቋንቋዬ እንዲተረጎም እንዴት መጠየቅ እችላለሁ?

## ጥያቄዎች ልዩ ፍላጎቶች ያለው/ላት ልጅ ቤተሰቦች

- ☐ ልጄ የእድገት መዘግየት እንዳለው/ላት ከጠረጠርኩኝ፣ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጋቸው ለመወሰን የትምህርት ቤቱ ሂደት ምንድን ነው?
- ☐ ልጄ ግለሰባዊ የትምህርት እቅድ(IEP) ወይም የ504 እቅድ አለው/ላት። አሁን ካሉበት ትምህርት ቤት ወደ ትምህርት ቤታችሁ የሚያደርጉትን ሽግግር ለመቆጣጠር ከእኔ እና ከልጄ ጋር እንዴት ትሰራላችሁ? እንደ ልጄ ተመሳሳይ አካል ጉዳተኝነት ያላቸው ተማሪዎችን ትምህርት ቤታችሁ እንዴት ይደግፋል?
- ☐ ልዩ ፍላጎቶች ላላቸው ልጆች የባህሪ ቁጥጥርን በምን አቀራረብ ትሄዱበታላችሁ? የባህሪ መቆጣጠር ጉዳዮች የሚያጋጥሟቸው ተማሪዎችን ለማገዝ ምን ዓይነት የድጋፍ ሥራተኛ አለ?
- ☐ የትምህርት ቤት የመስክ ጉዞ ላይ አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ልጆች የሰራተኛ ቻፔሮን አለ?
- ☐ ልዩ ፍላጎቶች ላላቸው ልጆች ራሱን-የቻለ ክፍል አላችሁ ወይስ አካታች ትምህርት ክፍሎችን ታቀርባላችሁ?
- ☐ ለሰራተኞች ሙሉ-ጊዜ ቴራፒስት አላችሁ (የስራ፣ የንግግር፣ አካላዊ)?
- ☐ የIEP ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? በምስክር ወረቀቱ ፕሮግራም ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ምን መርሃ-ግብር እና ትምህርቶችን ትሰጣላችሁ?

## ለቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት 3 ወይም ለቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት 4 እያመለከቱ ነው? ከታች ያሉ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ያስቡ

- ☐ የሙሉ-ጊዜ ፕሮግራም ታቀርባላችሁ ወይስ የግማሽ-ቀኖች አሏችሁ? ትምህርት ቤታችሁ የግማሽ-ቀኖች ሲኖሩት የበፊት እና የኋላ እንክብካቤ ታቀርባላችሁ?
- ☐ የቀናችሁ መዋቅር ምንድን ነው? ለምሳሌ፣ የጨዋታ ጊዜ፣ የቀን-እንቅልፍ ጊዜ ታካትታላችሁ?
- ☐ ልጄ ለሽንት ቤት የሰለጠነ/ች መሆን አለበት/ባት? የሽንት ቤት ስልጠና ላይ ፖሊሲያችሁ ምንድን ነው?
- ☐ ልጄ ከቀን-ውሎ እንክብካቤ/ሔድ ስታርት ወደ ቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት እየተሸጋገረ/ች ነው። ልጄ ሽግግሩን በሚያደርግበት/በምታደርግበት ጊዜ፣ ምን ዓይነት ድጋፍ ለልጄ ታቀርባላችሁ?
- ☐ ልጄ ግለሰባዊ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ (IFSP) አለው/ላት። ልጄ ወደ ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ለመሸጋገር ከእኔ እና ከልጄ ጋር እንዴት ትሰራላችሁ?
- ☐ ለቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት (PK3-PK4) የክትትል ፖሊሲያችሁ ምንድን ነው?

## ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ከ መዋዕለህጻናት-5) እያመለከቱ ነው? ከታች ያሉ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ያስቡ

- ◻ ትምህርት ቤታችሁ የሙሉ-ጊዜ የ5ኛ ክፍል አማካሪ አለው?
- ◻ ልጄ ከቀን-ውሎ እንክብካቤ/ሔድ ስታርት ወደ ቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት እየተሸጋገረ/ች ነው። ልጄ ሽግግሩን በሚያደርግበት/በምታደርግበት ጊዜ፣ ምን ዓይነት ድጋፍ ለልጄ ታቀርባላችሁ?

## ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ከ6-8 ክፍሎች) እያመለከቱ ነው? ከታች ያሉ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ያስቡ

- ◻ ተማሪዎችን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ከዚያ በላይ እንዴት ታዘጋጃላችሁ?
- ◻ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማመልከቻ ሂደት ውስጥ 8ኛ ክፍሎችን ለመደገፍ ምን ዓይነት ሰራተኞች እና ቁሳቁሶች አሉ?

## ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ከ9-12 ክፍሎች) እያመለከቱ ነው? ከታች ያሉ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ያስቡ

- ◻ ልጄ በትምህርታቸው አማካኝነት የኮሌጅ የትምህርት ሰዓትን መውሰድ ይችላል/ትችላለች?
- ◻ አማካሪ በኮሌጅ ማመልከቻዎች ላይ ልጄን ማገዝ ይችላል? የውትድርና ወይም የሙያ ዝግጅትስ?

## የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ፖሊሲዎች / ልምዶች

- ◻ ምን ዓይነት የቴክኒክ ድጋፍ ለተማሪዎች ታቀርባላችሁ (ለምሳሌ፣ ኮምፒውተሮች፣ MiFi)?
- ◻ ለተማሪዎች እና ሰራተኞች የCOVID-19 ፕሮቶኮሎች ምንድን ናቸው፣ የምርመራ ፕሮቶኮሎችን ጨምሮ? ለተማሪዎች እና ሰራተኞች የክትባት ፖሊሲያችሁ ምንድን ነው?
- ◻ ትምህርት ቤታችሁ በህዝብ ጤና ድንገተኛ አዋጅ ምክንያት መዘጋት ካለበት ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች የሽግግር እቅድ አላችሁ? ለውጦችን ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር እንዴት ትነጋገራላችሁ?
- ◻ ትምህርት ቤታችሁ ለሁሉም ተማሪዎች የፊት መሸፈኛዎችን፣ የእጅ ንጽህና መጠበቂያዎችን እና ሌሎች የመከላከያ መሳሪያዎችን ያቀርባል?
- ◻ ጭምብል መልበስ እና ሌሎች የመከላከያ መሳሪያዎች ላይ የትምህርት ቤታችሁ ፖሊሲ ምንድን ነው? እንዴትስ ይተገበራል?

